# የአቶ በርሄ ተክለጊዮርጊስ አጭር የሕይወት ታሪክ



1947 -1998 ዓ.ም

1954 - 2006

አቶ በርሄ ተክለጊዮርጊስ ከአባቱ ከአቶ ተክለጊዮርጊስ ይትባረክ እና ከእናቱ ከወ/ሮ ብርሃን ፍቃዱ በመቀሌ ከተማ ሰኔ 30 1947 ዓ.ም. ተወለደ። በቤተሰብ ፍቅርና እንክብካቤ ከአምስት ወንድሞቹና ከሦስት እህቶቹ ጋር በተወለደበት ከተማ ካደገ በኋላ፤ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በአጼ ዮሐንስ ትምህርት ቤት ውስጥ የአንደኛ ደርጃ ትምህርቱን አጠናቆ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እየተከታተለ በነበረበት ጊዜ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ይሄድ በነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ተሳታፊ ከመሆን አልፎ ቀንደኛ መሪ በመባል በወጣትነት ዕድሜው እሥር ቤት ተወረወረ።

በቤተሰብ ጥረት ከእሥር ከተለቀቀ በኋላ ባደገበት ከተማ የመኖር ዕድሉ አስተማማኝ ስላልሆንለት፤ ከወልጆቹና ከሚወዳቸው ወንድሞቹና እህቶቹ እንዲሁም ከጓደኞቹ ተለይቶ ወደ ዱፍቲ (ወሎ) በመሄድ በተንዳሆ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ።

በወጣትነት እድሜው በደሙ ውስጥ የተሰርፀው የሀገር እና የወገን ፍቅር እየገፋፋው ባለበት ዘመን የ1966 ዓ.ም. ህዝባዊ አብዮት መላ ኢትዮጵያን ሲያጥለቀልቅ፤ ወጣቱ በርሄ  የሠራተኞች ንቅናቄ አባል ሆነና መላ ሕይወቱ አደጋ ላይ ወደቀ። በዚሁ የተነሳ ውድ አገሩን ለቆ በመጀመሪያ ወደ ጂቡቲ ከዚያም ወደ መካከልኛው ምሥራቅ በመሰደድ የትግል ሕይወትን ቀጠለ።

በ1969 ዓ.ም. በኤርትራ በኩል ተጉዞ ወደትግራይ በመግባት የኢሕአፓን ሠራዊት ኢህአሠን ተቀላቀለ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል እሳካሁን ባደረገው ጉዞ  በርሄ ተክለጊዮርጊስ አብዛኛውን የለጋ ዘመኑን በማበርከት የሚፍለግበትን ድርሻ የተወጣ ኢትዮጵያዊ ጀግና ነው።

በጎንደር ክ/ሀገር በፀረ ደርግ ትግል ይንቀሳቀስ በነበረበት ጊዜ በደርግ ተይዞ ከፍተኛ እንግልትና ችግርን ካሳለፈ በኋላ አምልጦ ወደ ሱዳን ለመሰደድ ቻሏል።

በ1983 ዓ. ም. (እ.ኤ. አ.) ከባለቤቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር ወደ አሜሪካን አገር ተሰዶ በDallas, TX ከዚያም በSanjose, Ca ከቆየ

በኋላ ሦስተኛ ልጁንና ባለቤቱን ጨምሮ ወደ seattle ከተማ በመዛወር በሕይወት እስከተለየበት ዕለት ድረስ ኖረ።

በ2000 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በልጁ ስም የተሰየመውን ሣባ ሬስቶራንትን ከፍቶ ራሱን እና ቤተሰቡን ሲያስተዳድር ቆይቷል።

በርሄ በሩህሩነቱ፤ በቅንነቱና በሀገር ወዳድነቱ ሁሉም የሚያከብረውና የሚወደው ኩሩ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ በጓደኞቹና በሚያውቁት ሁሉ ዘንድ ታላቅ አክብሮትን አትርፏል።

ከስድስት ወራት በፊት ወደአገሩ ወደኢትዮጵያ ሄዶ ከእናት አባቱና ከመላው ቤተሰቡ ጋር ከቆየ በኋላ Feb 05, 2006 ወደሚኖርበት ወደ ሲያትል ከተማ ተመልሶ በመጣ በአምስተኛው ቀን በደረሰበት የጤና መታወክ የተነሳ ዕሑድ Feb 12, 2006 ከዚሕ ዓለም ከመካከላችን በሞት ተለይቶናል።

የዋሁ በርሄ

ገራገሩ በርሄ

አገር ወዳዱና ቁርጠኛው በርሄ በሁላችንም ልብ ውስጥ ለሁሌም ይኖራል።

መላ አዘነተኞች፤

ስላጽናናችሁን እናመሰግናለን፤

ከመከራ ይሰውራችሁ እንላለን፤

እግዚአብሄር ሁላችሁንም ይባርክልን።